የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.62
ADDIS ABABA 13th July, 2020

ማውጫ

Content

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፩/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነድ አዋጅ ….ገጽ ፲፪ሺ፮፻፸፬

Proclamation No.1211/2020

Special Government Bond Proclamation…Page 12,674

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፩/፪ሺ፲፪**

**ስለልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች (ቦንዶች) የወጣ አዋጅ**

የኢትዮጵያ ልማት ባንክን ካፒታል ለማሳደግ የሚውለው ገንዘብ በልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነድ (ቦንድ) እንዲከፈል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፩/፪ሺ፲፪” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስትሩ ፡-

፩/ ብር ፳፩ ቢሊዮን ፳ ሚሊዮን (ሃያ አንድ ቢሊዮን ሃያ ሚሊዮን) ዋጋ ያለው ልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነድ እንዲያወጣ፣

**PROCLAMATION NO. 1211/2020**

**SPECIAL GOVERNMENT BOND PROCLAMATION**

WHEREAS, it has become necessary to issue Special Government Bond to be used for raising the capital of the Development Bank of Ethiopia,

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**PART ONE**

**GENERAL**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the “Special Government Bond Proclamation No.1211 /2020”.

**2. Power of the Minister of Finance**

The Minister of Finance is hereby empowered:

1/ to issue Special Government Bond in the amount of Birr 21,020,000,000 (Twenty One Billion Twenty Million);

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነድ የኢትዮጵያ ልማት ባንክን ካፒታል ለማሳደግ እንዲያውል፣

በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ክፍያና ወለድ**

**፫. ክፍያ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚወጡት ልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች ከአምስት ዓመታት የችሮታ ጊዜ በኋላ በ፲፬ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ተከፍለው ይጠናቀቃሉ፡፡

**፬. ወለድ**

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡት ልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች ወለድ አይከፈልባቸውም፡፡

**ክፍል ሶስት**

**ልዩ ልዩ**

**፭. ከቀረጥና ግብር ነፃ መሆን**

ከልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች (ቦንዶች) ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ወይም ሰነዶች ላይ የቴምብር ቀረጥ ወይም ሌላ ማናቸውም ቀረጥና ግብር አይከፈልም፡፡

**፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2/ to utilize the Special Government Bond issued in accordance with this Proclamation to raise the capital of the Development Bank of Ethiopia.

**PART TWO**

**REDEMPTION AND INTEREST**

**3. Redemption**

Special Government Bond issued in accordance with Article 2 above shall be redeemed in 14 years period after a grace period of five years.

**4. Interest**

Special Government Bond issued in accordance with this Proclamation shall bear no interest.

**PART THREE**

**MISCELLANEOUS**

**5. Exemption From Taxes**

No Stamp duty or any other tax shall be levied on any transaction or document relating to the Special Government Bonds.

**6. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force as of its publication in the *Federal Negarit Gazette*.

**Done at Addis Ababa, on this 13th day of July, 2020**

**SAHILEWORK ZEWDW**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**